ቁጥር- ሽ1162/11/14688

መስከ 0 3 2016

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ለአንድ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

ቦርዱ በኢትዮጵያ ምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 100/2/ እና በመመሪያ ቁጥር 16/2013 በተሰጠው ስልጣን መሠረት መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሰጠውን የ2015 በጀት 2,750,873.43 /ሁለት ሚሊዮን ሰባ መቶ ሀምሳ ሺ ስምንት መቶ ሰባ ሶስት ከአርባ ሶስት/ ፓርቲው ለዚህ አላማ በከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ አድርጓል።

ፓርቲው በአዋጅ 1162/2011 በተጣለበት ሃላፊነት መሰረት የኦዲት ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን በኦዲት ሪፖርቱም ፓርቲው በዓመት ውስጥ ያደረጋቸው የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ቢሆንም ከእንቅስቃሴዎቹ ጋር የሚመጣጠን፦

- የሂሳብ አሰራር ስርዓት አልዘረጋም፤
- የቼክ እና የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ስርዓት አልዘረጋም፤
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አልተዘጋጀም፤
- የሂሳብ መግለጫዎቹ የተዘጋጁት በዓመቱ መጨረሻ ላይ በተዘጋጀ ደጋፊ ሰነዶች መሰረት ነው፤
- ፓርቲው የእንቅስቃሴዎቹን ከፊል ወጪዎች የሸፈነው ከግለሰቦች ባገኘው ብድር እንደሆነ ሂሳቡን በሂሳብ መዝገብ ላይ ማየት ስላልቻልን የብድሩን ትክክለኛነት አላረጋገጥንም የሚሉ ናቸው::

በሌላ በኩል የፓርቲው አባል በጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የፓርቲው የ2015 በጀት አጠቃቀምን በተመለከተ ባቀረቡት ቅሬታ በጀቱ ለፓርቲው ያልዋለ እና በተለያየ ምክኒያት በሊቀመንበሩ ብድር እየተባለ ለግል አገልግሎት እየዋለ በመሆኑ፤ ለሴቶች



ለድምጽዎ የሚያምኑን

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር
@NEBEthiopia
ኢሜይል
contact@nebe.org.et
ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ
+251 115 153468
ፋክስ
+251 115 510025

የተለያዩ ስልጠና የገባውን ገንዘብ በሊቀመንበሩ ለግል ጥቅም እየዋለ ስለሆነ ሂሳቡ እንዲጣራ ጠይቀዋል።

በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 82/6/ መሰረት ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊጠይቅ እንደሚችል በተደነገገው መሰረት የፓርቲው ሂሳብ እንዲጣራ ወስኖ በህዳር 12 ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር አ1162/11/1478 ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ሂሳቡን ተመርምሮ እንዲቀርብ አሳውቋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር በየካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር ፌ.ዋ.ኦ 98/2332 በተጻፈ ሪፖርት፡-

## I. <u>በመመሪያ ቁጥር 16/2013 አንቀጽ 7.2 መሰረት ፓርቲው የበጀት ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ የግልጽነትና ተጠያቂነት ሥርዓት ያልዘረጋ ስለመሆኑ</u>፡-

1. ፓርቲው ከመንግስት የተሰጠውን የድጋፍ በጀት በተመለከተ በየወጪ ሂሳብ መደቡ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር በመክፈት እንቅስቃሴውን የማይመዘግብ መሆኑ፤
2. ወጪ ወይም ግዴታ የሚገባበት ሂሳብ ከመፈቀዱ እና ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ የሚረጋገጥበት አሰራር አለመኖሩ፤
3. የግዢ ትእዛዝ የተሰጠበት ገንዘብ መጠን ለፓርቲው ከተሰጠው የበጀት ድጋፍ ላይ እየተቀነሰ የሚሄድበት አግባብ አለመኖሩ፤
4. ማናቸውም ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ የሚረጋገጥበት አሰራር አለመኖሩ እና
5. ማንኛውም ወጪ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ ቀርቦ ስልጣን ባለው የፓርቲው አመራር የሚፈቀድበት አሰራር አለመኖሩ እና ሌሎች የፋናንስ ቁጥጥር ስርዓቶች በፓርቲው ተግባራዊ ያልተደረጉ መሆናቸው በኦዲት ተረጋግጧል።

ጉዳዩን በተመለከተ ለፓርቲው በቀረበው የኦዲት መተማመኛ የፓርቲው ዋና ፕሬዝዳንት መመሪያ ከቦርዱ እንዳልደረሳቸው፤ የበጀት ድጋፍ ሲሰጣቸው በየበጀት አርዕስቱ ባለመሆኑ በጥቅል የተላከው መሆኑን፤ ክፍተቱን በቀጣይ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር በማዘጋጀት የሚሰሩ መሆኑን ለኦዲት መ/ቤቱ ቢገልጹም መመሪያው ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የደረሳቸው መሆኑና የበጀት ድጋፉን የሚጠቀሙበት አቅጣጫ እንደተሰጠ ከቦርዱ ባገኘው ማስረጃ ማረጋገጡን በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

## II. <u>ፓርቲው የተሰጠውን የድጋፍ በጀት በተለያ መዝገብ በወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መዝግቦ የማይዝ መሆኑ፤</u>

ፓርቲው በ2015 በጀት ዓመት ከመንግስት ከተሰጠው ድጋፍ 2,750,873.45 ብር ውስጥ 2,538,729.49 ወጪ አድርጎ መጠቀሙን እና የወጪውን ሂሳብ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ ያልያዘ መሆኑ በኦዲት መረጋገጡን፤ የፓርቲው ፕሬዝደንት በቀረበው የኦዲት መተማመኛ በሰጡት ምላሽ በመመሪያ ቁጥር 16/2013 አንቀጽ 20/2/ መሰረት የተሰጣቸውን በጀት ድጋፍ በየወጪ አርዕስቱ መዝግቦ አለመያዝ የተባለውን በተመለከተ እንደትልቅ የበጀት መስሪያ ቤት በሂሳብ መደብ አንመዘግብም እንጂ በየወጪ አርዕስቱ በኤክሴል እንደሚመዘግቡ፤ በየዓመቱ በሂሳብ ባለሙያ የተሰራ ሪፖርት ለቦርዱ እንደሚያቀርቡ፤ በተሰጠው አስተያየት መሰረት በቀጣይ እንደሚያስተካክሉ እንዳስረዱ ነገር ግን በኤክሴል ተመዘገበ የተባለው ለኦዲት መተማመኛ ምላሽ እንዲሆን የተዘጋጀ እንጂ አስቀድሞ በተሟላ ሁኔታ የተመዘገበ አለመሆኑን በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

## III. <u>ደጋፊ ሰነድ የሌላቸው እና በሚመለከተው የፓርቲው አመራር ዕውቅና ያላገኙ እና ያልጸደቁ ወጪዎችን በተመለከተ፤</u>

በመመሪያው አንቀጽ 7/2/ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጣቸውን የበጀት ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት እንዳለባቸው፤ በአንቀጽ 7/5/ ደግሞ ፓርቲው ሂሳቡን በህግ መሰረት ማንቀሳቀስ

እንዳለበት እና ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ እንደማይችል ይገልጻል። ከዚህ አንጻር ፓርቲው በ2015 ከተሰጠው በጀት ድጋፍ ውስጥ 655,415.81 ብር ለምን እንደዋለ ደጋፊ ማስረጃ የሌለው፤ በሚመለከተው የፓርቲው አመራር ወጪዎቹ ዕውቅና ያላገኙና ያልጸደቁ መሆናቸው በኦዲት ተረጋግጧል።

ጉዳዩን በተመለከተ የፓርቲው ፕሬዝደንት በኦዲት መተማመኛ ላይ በሰጡት ምላሽ ማንኛውም ወጪ ከፓርቲው አመራር ዕውቅና እንደማይወጣ፤ ነገር ግን በእያንዳንዱ ጥቃቅን ወጪ ላይ የአጽዳቂና ፈራሚ ቅጽ ተዘጋጅቶ በአጽዳቂ ተፈርሞ ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ወጪ የምናያይዝ ስለሆነ ክፍተቱን እናስተካክላለን ማለታቸው ግኝቱን የተቀበሉ እንደሆነ እንደሚያሳይ ነገር ግን ማንኛውም ወጪ ትክክለኛ ደረሰኝ ቀርቦ ነው ወጪ የተደረገው የሚለው በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት አለማግኘቱን ሪፖርቱ ያመለክታል።

## IV. <u>ከፓርቲው የቡና ባንክ ሂሳብ በባንክ ስቴትመንት መሰረት ከሀምሌ 2014 እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም ወጪ ሆኖ ነገር ግን ለምን ዓላማ እንደዋለ ማስረጃ ያልቀረበበትን በተመለከተ፤</u>

ፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚያገኙትን የበጀት ድጋፍ በመመሪያው አንቀጽ 10/2/ መሰረት ዜጎች በሀገራቸው የፖለቲካ ጉዳዮች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማድረግ፤ የፓርቲውን ዓላማ ለህዝብ ለማስተዋወቅ፤ የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማድረግ፤ የአባላት እና ደጋፊዎች ኃላፊነትና ግዴታዎችን ለማስተማር፤ ህብረተሰቡ የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን መብቱንና ግዴታውን እንዲወጣ ትምህርትና መረጃ ለመስጠት፤ የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች የእኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የፓርቲውን ዕጩዎች እና ወኪሎች ለማሰልጠን ዓላማዎች መዋል እንዳለባቸው ይገልጻል። ነገር ግን የቡና ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1029601000886 በተለያየ ጊዜ በባንክ ስቴትመንት መሰረት ወጪ የሆነው ገንዘብ ብር 2,707,678.55 ሲሆን በሰነድ ወጪ ሆኖ የተረጋገጠው 2,538,729.49 ብር በልዩነት ብር 168,949.06 ፓርቲው ለምን አላማ እንዳዋለው የሚገልጽ ማስረጃ የሌለው መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል። የፓርቲው ፕሬዝደንት በቀረበው የኦዲት መተማመኛ ላይ በሰጡት ምላሽ

ማንኛውም ወጪማስረጃ ሰነድ ሳይኖረው የወጣ ወጪ የለም ያሉ ቢሆንም በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ተቀባይነት እንዳላገኘ ሪፖርቱ ያስረዳል።

## V. ብድር ተመላሽ ተብሎ ከፓርቲው የባንክ ሂሳብ ወጪ ሆኖ ለፓርቲው አመራሮች የተከፈለውን ክፍያ በተመለከተ፤

ፓርቲው የብድር ተመላሽ በማለት ለአቶ ሲሳይ ደጉ 443,184 ብር፤ ለኢንጅነር አልአዛር አባይነህ 51,100 ብር፤ ለመምህር ሰለሞን አኒባል 10,000 ብር በድምሩ 504,184 ብር ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም፡-

- ፓርቲው ብድር እንደሚያስፈልገው ተወያይቶ ብድር መበደር እንዳለበት በቃለ-ጉባኤ ያጸደቀበት ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- ፓርቲው ከግለሰቦች ጋር የተፈራረመው የብድር ውል የሌለ መሆኑን፤
- በብድር ውል ስምምነት ገንዘቡ ወደ ፓርቲው የባንክ ሂሳብ የገባበት የባንክ ክሬዲት አድቫይስ የሌለ መሆኑን፤
- ብድሩ ወደ ፓርቲው የባንክ ሂሳብ ገቢ ሲደረግ የተቆረጠ የገቢ ደረሰኝ የሌለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል።

በቀረበው የኦዲት መተማመኛ ላይ የፓርቲው ፕሬዝደንት በሰጡት ምላሽ ግኝቱ ትክክል መሆኑን፤ በጀት እስከሚሰጠን ድረስ ለቤት ኪራይ እና ለሰራተኛ ደሞዝ እንዲሁም ለስራ ማስኬጃ የወጡ ወጪዎች እንደሆኑ፤ በጀት እስከሚለቀቅ ፓርቲዎች ተበድረው እንዲሰሩ በሚል አሰራር በቦርዱ እንዳለ፤ የብድር ውል እና ክሬዲት አድቫይስ ሊኖር ይገባ እንደነበር፤ በቀጣይ እንደሚያስተካክሉም መግለጻቸውን። ያለአግባብ ወጪ ሆኖ የተወሰደው ገንዘብ ወደ ፓርቲው የባንክ ሂሳብ ተመላሽ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት መመዝገብ አለበት።

እንዲሁም ለኦዲት ግኝቱ የተሰጠው ምላሽ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን እና የተጠቀሰው ገንዘብ ከፓርቲው የባንክ ሂሳብ ወጪ እንዲደረግ ቼክ የፈረሙት አቶ ሲሳይ ደጉ ድልአርጌ የፓርቲው ፕሬዝደንት፤ አቶ ሰለሞን አኒባል አድከስ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት እና ወ/ሮ ሙሉ አመንሲሳ ሳኤርባ መሆናቸው በኦዲት ተረጋግጧል ሲል በሪፖርቱ ገልጿል።

## VI. ከየካቲት 8 ቀን 2015 ዓ.ም እሰከ ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም በተለያዩ ጊዜያት ለስልጠና እና ለውሎ አበል የተከፈለን ክፍያ በተመለከተ፤

ፓርቲው ከየካቲት 8 ቀን 2015 ዓ.ም እሰከ ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለስልጠና እና ለክልል ወኪሎች ውሎ አበል ብር 1071428.90 ወጪ ሆኖ የተከፈለው ገንዘብ የተቀባይ ፊርማ እና ሲከፈል ከፓርቲው አካውንት ተቀናሽ ተደርጎ ወደ ተከፋዩ አካውንት ገቢ እንዲደረግ ለባንክ የተጻፈ ደብዳቤ የሌለ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ለፓርቲው በቀረበ የኦዲት መተማመኛ የፓርቲው ፕሬዝደንት በሰጡት ምላሽ ለባንክ የተጻፈ ደብዳቤ የለም የተባለውን በተመለከተ አሰራራችን ከባንክ ወደ ተከፋዩ አካውንት የገባበት ማስረጃ ያለ በመሆኑ የባንክ አካውንት የሌላቸውን በማስፈረም የሰጠን ሲሆን የባንክ አካውንት ላላቸው ደግሞ ከባንክ ወደ ባንክ የከፈልንበት አያይዘናል፤ አንዳንድ ክፍተቶቻችንን የምናስተካክል መሆኑን እና ከባንክ ወደ ባንክ የተሟላ ክፍያ እና ከምርጫ ቦርድ በሚሰጠን አቅጣጫ መሰረት እንሰራለን ማለታቸውን ነገር ግን ከባንክ ወደ ተከፋዩ አካውንት የገባበት ማስረጃ ያልቀረበ እና አካውንት የሌላቸውን በማስፈረም ሰጥተናል ያሉት ደግሞ ከግኙቱ ጋር የማይገናኝ/በግኝት የተያዘው ገንዘብ ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ የተወሰደ ፊርማ ስለሆነ ለግኙቱ የተሰጠው ምላሽ በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም የሚል ነው፡፡

ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረበውን የዋና ኦዲተር ሪፖርትና ፓርቲው ለዋና ኦዲተር የሰጠውን መልስ ቦርዱ መርምሯል፡፡ እንደሚታወቀው በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 102/2/ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የተሰጣቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን የሚያሳውቁበት የግልጽነትና የተጠያቂነት መርህ መከተል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች አግባብ ባለው ህግ መሰረት ሂሳቡን ማንቀሳቀስ፤ ድጋፉን በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ እና በበጀት ዓመቱ ከመንግስት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምነ ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር ወይ በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለባቸው አንቀጽ 105 /ሀ-መ/ ይደነግጋል፡፡

በተመሰሳይ መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 16/2013 አንቀጽ 7/2 እና 5/ ፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፉን በአግባቡና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት እንዳለባቸው እንዲሁም ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ሂሳቡን በህግ መሰረት ማንቀሳቀስ እንዳለበት፤ ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ እንደማይችል ግዴታ ተጥሎበታል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጣቸውን የበጀት ድጋፍ በአንቀጽ 10 /2ሀ-ሸ/ የተዘረዘረ ሲሆን ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ከታለመለት አላማ ወጪ ከዋለ በአዋጁ አንቀጽ 106 እና በመመሪያው አንቀጽ 25 መሰረት ቅጣት ሊጣልበት እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል። በመሆኑም ፓርቲው ያቀረበው የ2015 ኦዲት ሪፖርት እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያቀረቡት የኦዲት ግኝቶችን በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት የተሰጠውን ገንዘብ የፓርቲውን አላማ ለህዝቡ ለማስተዋወቅ፤ ዜጎች በአገራቸው የፖለቲካ ጉዳዮች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማድረግ፤ የመራጩን ህዝብ የፖለቲካ ግንዛቤና እውቀት እንዲዳብር ለማድረግ፤ የሴቶችና የአካል ጉዳተኛ ዕጩዎችን የእኩል ዕድል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤ ህብረተሰቡ የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን መብቱንና ግዴታውን እንዲወጣ ትምህርትና መረጃ ለመስጠት እና ለመሰሰሉት ተግባራት መዋል እያለበት ከዚህ ውጪ በፓርቲው አመራሮች የፋይናንስ አሰራርን በልተከተለ መንገድ ገንዘቡ ለግል ጥቅም ሲውል እንደነበር፤ የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ ስርዓት ያልተዘረጋለት እና በማስረጃ ያለተረጋገጡ ከፍተኛ ወጪዎች መኖራቸውን ከቀረበው የኦዲት ግኝት በርዱ መረዳት ችሏል።

በተጨማሪ ፓርቲው እነዚህን ብድሮች እና ያለህጋዊ ማስረጃ ጭምር የወጡ ከፍተኛ ወጪዎች ተገቢውን የሂሳብ አሰራር ስርዓት ተከትሎ እንዳልፈጸመ እና ብድር በማለት በፓርቲው ሃላፊዎች የተወሰደውንም ገንዘብ ይህንን የሚፈቅድ የቦርድ አሰራር በሌለበት እንዳለ ለማስመሰል መሞከሩ ፈጽሞ የህግ ተቀባይነት የለውም። እንዲሁም ከፍተኛ

የሚባሉ ወጪዎችን ጥቃቅን ወጪዎች በማለት ለእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ ግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር በለመዘርጋት እንደውም ወደፊት የማስተካከል እቅድ እንዳለው የገለጸበት አግባብ በአዋጁ የተጣለበትን የሂሳብ አሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋ ያመነ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በዚህ መሰረት ፓርቲው በ2015 ዓ.ም በቦርዱ የተደረገለትን የበጀት ድጋፍ ለታለመለት አላማ እንዳላዋለ እና ከፍተኛ ገንዘብ በፓርቲው አመራሮች እና ለሌሎች አባላት የግል ጥቅም እንዲውል መደረጉን ቦርዱ ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ቦርዱ የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በአካሄደው ስብሰባ በፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት ላይ የተዘረዘሩትን የፓርቲው አመራሮች እና ፓርቲውን በተመለከተ ፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 106/1ለ/ መሰረት ተገቢው የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 106/2/ መሰረት አላግባብ ወጪ የሆነው ገንዘብ በተመለከተ የፍ/ብሄር ክስ እንዲመሰረት እና ገንዘቡ ለቦርዱ ተመላሽ እንዲደረግ፤
3. በአዋጁ አንቀጽ 98/3/ መሰረት በፓርቲው አመራሮች የተፈጸመው የወንጀል ተግባር ተጣርቶ እስከሚቀርብ ድረስ ፓርቲው እና አመራሮቹ እንዲታገዱ መወሰኑን እናሳውቃል፡፡

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board